## *በወንጌል የተገለጠው የእግዚአብሔር ፅድቅ ዘላለማዊ ወዋስትና*

**ንባብ ሮሜ8:31-39**

**ዓላማ:-**

- በወንጌል የተገለጠው የእግዚአብሔር ፅድቅ ዘላለማዊ ዋስትና አለው።

- በወንጌል የተገለጠው ፅድቅ መሰረቱ የክርስቶስ ኢየሱስ ድል አድራጊነትና የማይለወጠው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው።

- በወንጌል የተገለጠው የእግዚአብሔር ፅድቅ በክርስቶስ ምልጃ/ መካከለኛነት የተከናወነ ነው።

***መግቢያ:-*** በቀደመው ትምህርት በወንጌል የተገለጠው የእግዚአብሔር ፅድቅና የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ አላማ በተመለከተ ተምረን ነበር።በዛሬው ትምህርት ደግሞ ይህ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አላማ ዋስትናው ምን እንደሆነ እንማራለን።

**1:የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ ልዋልዐዊነቱ። ሮሜ 8:31-33**

1:1 ማንም ሊቃወመው አይችልም።

1:2 ልጁን ስለ ሁላችን አሳልፎ ለመስጠት አስችሎታል።

1:3 እግዚአብሔርን ብቻ የሚፅድቅ አድርጎታ።

**2: የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ መሰረት ምንድ ነው? ሮሜ 8:33-34**

2:1 የክርስቶስ ኢየሱስ ሞት ነው

2:2 የክርስቶስ ኢየሱስ ትንሳኤ ነው

2:3 የክርስቶስ ኢየሱስ መክበር ነው።

2:4 የክርስቶስ ኢየሱስ ምልጃ ነው።

**3: የእግዚአብሔር ዘላለማዊ አላማ ምክንያት ምንድ ነው? ሮሜ 8:35-39**

3:1 በማንኛውም ችግር ውስተ ስናልፍ አይለወጥም።

3:2 በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የተገለጠ ነው።

***ማጠቃለያ***:-እግዚአብሔር በኃጢአት ምክንያት የጠፋውን ወይም የሞተውን የሰውን ልጅ ያዳነው በድንገት ሳይሆን በዘላለማዊ ሀሳቡና አላማው መሰረት ነው።ምክንያቱም ሰው  ህግን በመጠበቅም ሆነ በመልካም ስራው መፀድቅ አልቻለምና።ስለዚ እግዚአብሔር በልጁ ሰው መሆንና በቤዛነት ስራው በተገለጠው ፀጋው የራሱን ፅድቅ ቆጠረለት። ይህ የተቆጠረለት ፅድቅ  ደግሞ በእግዚአብሔር ሉዐላዊነት፣ በክርስቶስ ማንነትና የቤዛ ስራ እንዲሁም በማይለወጠው የእግዚአብሔር ፍቅር ላይ የተመሰረተና ዘላለማዊ ዋስትና ያለው ነው።በመሆኑም አማኝ አይጠፋም።ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።